የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No.11
ADDIS ABABA 2nd November, 2004

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፮/፲፱፻፺፯ዓ.ም

ለክብረመንግሥት ከተማ የውኃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ..... ገጽ... ፪ሺ፱፻፵፩

## CONTENTS

Proclamation No. 426/2004

Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for financing the Kibre Mengist Town Water Supply Project Ratification Proclamation. No. ....Page 2941

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፮/፲፱፻፺፯

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለክብረመንግሥት ከተማ የውኃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፮ሚሊዮን፪፻፵ሺ የአሜሪካን ዶላር (ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፱ ቀን ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኤኮኖሚ ዓለም ዐቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION NO. 426/2004.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of USD 6,240,000 (six million and two hundred forty thousand USD) for financing the Kibre Mengist Town Water Supply project, was signed in Addis Ababa on 9th day of July, 2004;

**WHEREAS,** basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 2nd day of November, 2004;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለክብረመንግሥት ከተማ የውኃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፮/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፱ ቀን ፪ሺ፬ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው::

## ፫. የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፮ሚሊዮን፪፻፵ሺ የአሜሪካን ዶላር (ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አርባ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for financing the Kibre Mengist Town Water Supply Project Ratification Proclamation No. 426/2004."

## 2. Definition

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa on the 9th day of July, 2004.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of (USD 6,240,000) six million and two hundred forty thousand USD) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the 2nd day of November, 2004.

**Done at Addis Ababa, this 2nd day of November, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**